በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፮


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:-** kesisolomon4@gmail.com


To get all the lessons, surf : www.zeorthodox.org

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ጥቅምት ፳ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም.**

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፺

- በምንኖርባት ዓለም መሪዎች እጅግ ከፍ ባለ መጠን ይፈለጋሉ፡፡ በመጽሐፈ ነህምያ ለማንኛውም ቤት፣ ድርጅት፣ ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጉ ዓይነት መሪዎች ምሳሌነት ተጽፎልናል፡፡
- ነህምያ የገጠሙትን ችግሮችና ፈተናዎች በመቋቋም ሕዝቡ በድኅነት ወደ ደቀቁባት ኢየሩሳሌም ተመልሶ ሕዝቡን አሳምኖና አስተባብሮ የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች ግንባታ ከግማሽ አደረሰው፡፡
- ይህ ሥራ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የምናገኘው ታላቁ የፕሮጀክት ሥራ ነው፡፡
- ባለፉት ጊዜያት ነህምያ በመነቀፍ እንዴት እንደተፈተነና በመነቀፍ ውስጥ ማለፍ ለመሪዎች የሚያስገኘውን ጠቀሜታ፣ ብሎም ተስፋ በመቁረጥ የገጠመውን ፈተና፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት በምንሰጠው አገልግሎት ይህ የሚጠብቀን ፈተና መሆኑንና እነዚህ ፈተናዎች የመሪዎች የሥራ ኃላፊነት ዝርዝር ውስጥ የምናገኛቸው ድርሻዎች እንደሆኑ ተመልክተናል፡፡
- ባለፉት ሁለት ሳምንታት ፈተናዎቹንና ሲገጥሙንም የምናደርጋቸው ነገሮች ወይም የምንወስዳቸው እርምጃዎች ምን እንደሆኑ ተመልክተናል፡፡
- ዛሬ የምንመለከተው በነህምያ የመሪነት ሕይወት ውስጥ የምንማርባቸውን ሌሎች ሁለት ገጽታዎች ነው፡፡
- እነዚህም ሁለት ገጽታዎች የገንዘብ ቀውስንና ስኬትን የተመለከቱ ናቸው፡፡
- የገንዘብ ቀውስ ሲገጥመን የምናደርገው ምንድር ነው? መሪዎች በ21ኛውን መቶ ክፍለ ዘመን የሥልጣኔ ቁንጮ የሆኑትን አገሮች የገንዘብ ቀውስ ችግር ለመፍታት ይህንን ምዕራፍ ቢያጠኑት ይጠቅማቸው ነበር፤ ምናልባትም እየሰሙን ሊሆኑ ይችላሉ!
- በመጽሐፈ ነህምያ የመጀመሪያዎቹን አምስት ቁጥሮች እናንብብና መሪው ነህምያ የገጠመውን የገንዘብ ቀውስ እንዴት እንደፈታና የመሪነት ብቃቱንም እንዳሳየ እንማራለን፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፤

- ‹‹በወንድሞቻቸውም በአይሁድ ላይ ትልቅ የሕዝቡና የሚስቶቻቸው ጩኸት ሆነ።›› ***ነህ 5፥1።*** እንዳለ ቅጥሩን ይሠሩ በነበሩት መካከል በድንገት ነውጥ ወይም አመጽ ተከሰተ፡፡ በዚህም የተነሣ የቅጥሩ ሥራ ተቋረጠ፡፡ ሕዝቡም እርስ በርሳቸው ተቀዋወሙ፡፡
- ‹‹አያሌዎቹም። ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችን ብዙዎች ናቸው በልተንም በሕይወት እንድንኖር እህልን እንሸምት ይሉ ነበር። አያሌዎቹም። ከራብ የተነሣ እህልን እንሸምት ዘንድ እርሻችንና ወይናችንን ቤታችንንም አስይዘናል ይሉ ነበር። ሌሎቹም። ለንጉሡ ግብር እርሻችንንና ወይናችንን አስይዘን ገንዘብ ተበድረናል አሁንም ሥጋችን እንደ ወንድሞቻችን ሥጋ፥ ልጆቻችንም እንደ ልጆቻቸው ናቸው እነሆም ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችን ባሪያዎች ይሆኑ ዘንድ ሰጥተናል፥ ከሴቶችም ልጆቻችን ባሪያዎች ሆነው የሚኖሩ አሉ ታላላቆችም እርሻችንና ወይናችንን ይዘዋልና ልናድናቸው አንችልም ይሉ ነበር።›› ***ነህ 1፥2-5።***
- ከወላጆቻችን የወረስነውን ቤትና ንብረት አስይዘን የረጅም ጊዜ ብድር ወስደናል፡፡ ብድሩንም የዘወትር ቀለባችንን ለመስፈር፣ ምግብ ለማግኘት አውለነዋል፡፡ የመንግሥት ግብር ለመክፈልም መሬታችንን - እርሻችንንና ወይናችንን አስይዘን ገንዘብ ተበድረናል… አሉ፡፡
- አሁን ሁሉን በብድር ዕዳ ስላስያዙና የሚያስይዙትም ስላጡ ራሳቸውን፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን እንደባሪያ አሳልፈው ሸጡ፡፡
- እስኪ ራሳችሁን ነህምያ አድርጋችሁ አስቡ! ቅጥሩ ተሰርቶ መካከል ደርሷል፣ አመጽ ወይም ነውጥ ተነሳባችሁ፡- ሕዝቡ የምንበላው፣ ለግብር የምንከፍለውም የለንም፣ ልጆቻችንም ባሮች ሆነዋል አሉ፡፡
- እናንተ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ብትሆኑ ምን ታደርጋላችሁ? አንዳንድ ሰዎች እንደሚያደርጉት በንግግር ብቻ ልታጽናኑአቸው ትሞክራላችሁ? ቅጥሩን እንዲገቡ ነሞራል ቀስቃሽ ንግግሮችን ታደርጉላቸዋላችሁ?

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፮

- ወይስ ወደዚህ ሰብሰብ በሉ፣ በቅድሚያ የቅጥሩን ሥራ ፈጽሙ፣ ከዚያ በኋላ የቤታችሁ ዋጋ ከፍ ይላል (ይጨምራል) - ሁሉ ነገር ይስተካከላል - ትላላችሁ? ወይስ ከንጉሡ ጥቂት ገንዘብ ለምናችሁ ታመጡላቸዋላችሁ?፣ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ብትሆኑ ምን ታደርጋላችሁ?
- ነህምያ ችግሩን በተመለከተ እጅግ የሚያስደንቅ ነገርን አደረገ፡፡ ‹‹ እኔም ጩኸታቸውንና ይህን ቃል በሰማሁ ጊዜ እጅግ ተቈጣሁ።›› ***ነህ 5፡6፡፡*** እርምጃ ከመውሰዱ በፊት ለማሰብ፣ ለጸሎት፣… ጊዜ ወስዷል፡፡ ጊዜ መውሰዱን ተከትሎም የተቆጣው በሕዝቡ አልነበረም፡፡
- የምሠራው የእግዚአብሔርን ሥራ ነው፤ ቅጥሩ ይሠራም ዘንድ እግዚአብሔር ፈቃዱ ነው፣ ይህም ሆኖ ሕዝቡ የሚበላው ነገር ካጣ እግዚአብሔር ሊነግረን የፈለገው ነገር አለ ማለት ነው አለ፡፡ እግዚአብሔር ሕዝቡን ያልመገባቸው ስለምንድር ነው? ሕዝቡ ስለምን ደኸዩ? ችግሩ ከምን የመጣ ነው? አለ፡፡
- እንደምናውቀው ነህምያ ‹‹ ወንድምህ ቢደኸይ እጁም በአንተ ዘንድ ቢደክም፥ አጽናው እንደ እንግዳና እንደ መጻተኛም ከአንተ ጋር ይኑር። ወንድምህ ከአንተ ጋር ይኖር ዘንድ ከእርሱ ምንም ወለድ ወይም ትርፍ አትውሰድ ነገር ግን አምላክህን ፍራ። ብርህን በወለድ አታበድረው መኖህንም በትርፍ አትስጠው።›› ***ዘሌዋ 25፡35-37፡፡*** የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል በደንብ ያውቀዋል፡፡ ‹‹ወንድምህን ባሪያ አታድርገው፤ ሆኖ ብታየውም ነጻ አውጣው›› እንዳለ ያውቅ ነበር፡፡
- ይበሉና ይኖሩ ዘንድ ለሚያስፈልጋቸው ወንድሞቻችንን በወለድ እንዳናበድራቸው እንጠንቀቅ፡፡ በርግጥ በቅድሚያ ለመንደላቀቅ፣ ወይም የምቾት መኪና ወይም ቁሳቁስ ለመግዛት እንደማይበደሩን እንወቅ፡፡
- በዚያ ዘመን ወለዱ ከባድ ነበር 50% ወይም 60% በላይ ይታሰባል፤ መክፈልም ሲያቅታቸው ባሪያ ይሆኑ ነበርና እግዚአብሔርም ‹‹ወንድምህም በወለድ አታበድረው አለ፡፡ አበድረው  ግን በወለድ አይሁን፡፡›› አለ፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፮

- ነህምያ ከሁሉ አስቀድሞ የሕዝቡ ችግር ከምን እንደመነጨ አጠና። የእግዚአብሔርንም ሕግ እየጠበቁ እንዳልሆነ አረጋገጠ፤ ሕዝቦቹ በየዕለቱ የእግዚአብሔርን ሕግ ስለሚተላለፉ የገንዘብ ቀውሱም ምንጭ ይህ ነበር።
- የገንዘብ ቀውስ ሲገጥመው ወደ እግዚአብሔር መመለስ አለብን አለ? ሁላችንም እንዲህ ያለው ቀውስ ከየት እንደሚመጣ ቁጭ ብለን ማሰብ ይኖርብናል። ነህምያ በተከተለው አቅጣጭ የደረሰበትን ተጨባጭ ነገር ልንመለከት ይገባናል።
- ‹‹በልቤም አሰብሁ፥ ታላላቆቹንና ሹማምቱንም። ሁላችሁ እያንዳንዳችሁ ወለድ ትወስዳላችሁ ብዬ ተጣላኋቸው ትልቅም ጉባኤ ሰበሰብሁባቸው። እኔም። ለአሕዛብ የተሸጡትን ወንድሞቻችንን አይሁድን በፈቃዳችን ተቤዠን እናንተስ ወንድሞቻችሁን ትሸጣላችሁን? እነርሱስ ለእኛ የተሸጡ ይሆናሉን? አልኋቸው። እነርሱም ዝም አሉ፥ መልስም አላገኙም። ደግሞም አልሁ። የምታደርጉት ነገር መልካም አይደለም ጠላቶቻችን አሕዛብ እንዳይሰድቡን አምላካችንን በመፍራት ትሄዱ ዘንድ አይገባችሁምን?›› ***<u>ነህ 5:7-9።</u>*** እጅግ የሚያስደንቀው መሪ ነህምያ በቀጥታ የችግሩን ቁልፍ ነገር አገኘ።
- የችግሩን ቁልፍ መፍትሔ የሚፈልገው የገንዘብ ማሰባሰቢያ መርሐ ግብር፣ ወይም ስሜት ቀስቃሽ ንግግር፣ ከውጪ የገንዘብ እርዳታ ማግኘት አይደለም፣ እነዚህ ሁሉ ችግሩን አይፈቱም፤ የሚፈለገው ንስሐ ነበርና።
- የገንዘብ ቀውስ ችግርን በንስሐ የሚፈታ ማነው? እግዚአብሔርን በመፍራት የሚራመድ ግቡንም በግልጽ የተረዳ መሪ ነው። ግቡ ቅጥሩን መሥራት አልነበረም፤ በምዕራፍ አምስት ቅጥሩ የቀረ ያህል ስለቅጥሩ አልተጻፈልንም። የነህምያ ግቡ እግዚአብሔርና የእግዚአብሔር ክብር ነው።
- ግቡ ሰንበት ት/ቤት፣ ሥርዓተ ትምህርቱ፣ የሚሠሩ ሥራዎች፣ የሚሰጡ አገልግሎቶች፣ ወዘተ አይደሉም፤ በመጨረሻ የእግዚአብሔር ክብር ነው እንጂ።

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፯

- ‹‹የእግዚአብሔርን ሕግና ሥርዓት ቃል ኪዳኑንም እየጣስን ቅጥሩ በፍጹም ግብ ሊሆነን አይችልም። ግቡ እግዚአብሔር ደስ ማሰኘትና እርሱንም በመፍራት መመላለስ ነው። ይህን እንዴት ልናደርው እንችላለን?›› አለ።
- ነህምያ ‹‹በወለድ ማበደርን፣ ወንድሞቻችሁንና እህቶቻችሁን ባሮች ማድረጋችሁን ተው›› አላቸው። *‹‹የምታደርጉት ነገር መልካም አይደለም ጠላቶቻችን አሕዛብ እንዳይሰድቡን አምላካችንን በመፍራት ትሄዱ ዘንድ አይገባችሁምን? ›› አላቸው።*
- መለወጥ ያለብን ስማችንን ያጠፋውን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ክብር የሚጋፋውን ነገር ነው። መለወጥ ማለት ‹‹እኛ እንዲህ ያለ ስም ይዘን እንዴት ይህን አደረጉ›› እንዳንባል ያህል ወይም ለስማችንና ለዝናችን ስንል አቅጣጫችንን መቀየር ሳይሆን የእግዚአብሔርን ክብር የሚቀናቀነውን ነገር መተው ነው።
- ነህምያ ‹‹ወንድሞቻችንንና እህቶቻችንን ባሪያ የምናደርጋቸው ከሆን ጠላቶቻችን ደስ ይላቸዋል፣ ስለዚህ አይገዳችሁም፣ ስለእግዚአብሔርስ ስምና ክብር አትቀኑም?›› አላቸው።
- በርግጥ የሚነጋገሩት የተለያየ ቋንቋ ነበር፤ እነርሱ የሚናገሩትና የሚያስቡት ስለ ገንዘብ ነው፣ እርሱ ደግሞ ስለ እግዚአብሔር ክብር ይነግራቸው ነበር።
- ኃጢአት በቤተ ክርስቲያን ሲነግስ የሚደሰተው ጠላት ነውና እንዲህ ያለውን ስድብ ማቆም አንሻም ይሆን?
- ነህምያም ‹‹እኔም ደግሞ ወንድሞቼም ብላቴኖቼም ገንዘብና እህል ለእነርሱ አበድረናል እባካችሁ፥ ይህን ወለድ እንተውላቸው። እርሻቸውንና ወይናቸውን ወይራቸውንና ቤታቸውንም ከእነርሱም የወሰዳችሁትን ገንዘቡንና እህሉን፥ ወይን ጠጁንና ዘይቱን ከመቶ እጅ አንድ እጅ እባካችሁ ዛሬ መልሱላቸው።›› ***ነህ 5:10-11።*** አላቸው።
- ነህምያ የገንዘብ ቀውስ የሚፈታው በንስሐ መሆኑንና ለዚሁም ዛሬ መወሰንና እርምጃ መውሰድ እንደሚያስፈልግ ተናገረ።

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፺

- ***የመጀመሪያውም እርምጃ <u>እርምት</u> ማድረግ ነው*** አላቸው፡፡
- ‹‹እርሱም፡- እንመልስላቸዋለን፥ ከእነርሱም ምንም አንሻም እንደ ተናገርህ እንዲሁ እናደርጋለን አሉ። ካህናቱንም ጠርቼ እንደዚህ ነገር ያደርጉ ዘንድ አማልኋቸው።›› ***<u>ነህ 5፡12፡፡</u>***
- **ከእርምት ቀጥሎ *<u>ታናዘዙ</u>* አላቸው፡፡ ኑዛዜያቸውንም በጉባኤ አደረጉ፤ ሲናዘዙ ሕዝቡ ሁሉ ይሰማቸው ነበር፡፡** ‹‹ደግሞም ልብሴን አራገፍሁና። ይህን ነገር የማያደርገውን ሰው ከቤቱና ከሥራው እንዲሁ እግዚአብሔር ያራግፈው እንዲሁም የተራገፈና ባዶ ይሁን አልሁ። ጉባኤውም ሁሉ። አሜን አሉ፥ እግዚአብሔርንም አመሰገኑ ሕዝቡም እንደዚህ ነገር አደረጉ።›› ***<u>ነህ 5፡13፡፡</u>***
- **ይህን የመሰለውንም ጥፋት ደግመው ላያደርጉትም *<u>ቃል ገቡ፡፡</u>***

1. **እስካሁን ከደረስንበት የምንማረው የመጀመሪያው ነገር እስራኤላውያን የገጠማቸውን የገንዘብ ቀውስ ከመስጠት ይልቅ ድሆችን የሚበረብሩትን ባለጠጎችን ንስሐ በማስገባት እንደፈቱት ነው፡፡** (በሕይወታችን ያለ ችግር በገንዘባችን *ታማኝ* ካልሆን - *አሥራቱን* ካልሰጠን አይፈታም - ድሆች የሚበሉት የሚገኘው ከርሱ ነውና - በርካታ ሰዎች ስለማይሰጡ የተባረኩ አይደሉም፤ ለምን እንዳልተባረኩም አያውቁም - እኛ በምቾትና ቅንጦት እየኖርን - በዚህ እየቀጠልንም ድሆች ወንድምና እህቶቻችንን ስለምናስርባቸው በረከቱ ይርቀናል)፡፡
2. ***ሁለተኛው ነገር መሪ ሌሎችን ለመምራት የመሰደባችን ምንጭ ከመሆን መጠንቀቅ አለበት፡፡ ነህምያ*** **በእግዚአብሔር ሕግ ስለኖረ እግዚአብሔርን መስማት ይችል ነበር፤** ***ለችግሩ መፍትሔ ለማግኘት*** **የቻለው የሕይወቱ ብርጭቆ ንጹሕ ስለነበር ነው፡፡ ሕግጋቱን እያፈረስን ሐሜት፣ ስካር፣ አመንዝራነት ሲሰለጥንብን ብርጭቆው እየጠቆረ ይሄዳል፡፡ ችግራችንንም ለይተን ማወቅ ይቸግረናል፡፡** ***ነገሩ*** **ሁሉ ግራ የተጋባ ይሆንብናል፤ የምንይዘውንና የምንጨብጠውንም እናጣለን፡፡**

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፺

- ነህምያ ብርጭቆ ሕይወቱ ንጹሕ ስለነበር ችግሩን ከምንጩ ነቅሶ ማውጣትና መፍትሔ ለመስጠት ችሎ ነበር፡፡
- እግዚብሔር ብዙ ጊዜ የሰዎችን ችግር እንድንፈታ ሊጠቀምብን ይችላል፤ ታዲያ እኛ ችግሩንና የችግሩን ምንጭ ማግኘት እንችላለን? እንዲቻለን በቅድሚያ በራሳችን ዓይን ያለውን ምሰሶ ማጽዳት አለብን፡፡
- ፍጹም ንስሐ ካልገባን፣ የንስሐንና የንጽሕናንም ሕይወት ካልኖርን ኤልያስንም ሆነ መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስን መሆን አንችልም፡፡ ካልሆነ እውራንን የምንመራ እውራን ሆነን እንገኛለን!!!
- ጌታችን ጻፎችና ፈሪሳውያንን አስመልክቶ መልካም መሪዎች እንዳልሆኑም ነግሮናል፡፡ ማቴ 23፡1-39፡፡
- መሪዎች ግልጽ ራዕይ እንዲኖራቸው ያስፈልጋቸዋል፡፡

3. ሦስተኛው ስለ ቅጥሩ ሥራ በዚህ ምዕራፍ ምንም ነገር አልተጻፈልንም፡፡ ለምን? ብስጭታችንና ቁጣችን እስኪበርድልን፣ ንስሐ እስክንገባበት፣ ችግራችንን ከውስጥ እስክንፈታው ድረስ አገልግሎታችንን ሳይቀር ማቆም እንደሚኖርብን ለማስተማር ነው፡፡ ካልሆነ ግን አሁንም እውራንን የምንመራ እውራን እንሆናለን፡፡

- በዚህ የተነሳ የቅጥሩን ሥራ አቁመውት ነበር፤ ሕዝቡ ካልበላ እንዴት ሊሠራው ይችላል? ‹‹አሁን ስለ ቅጥሩ አታስቡ፤ በቅድሚያ በውስጣችን ያለውን ኃጢአት በንስሐ እናስተካክል፡፡›› አላቸው፡፡

4. የመጨረሻው ነገር የተደበቀውን ኃጢአት ሳይፈራ ገልጦ ማውጣቱ ነበር፡፡ ነህምያ አላቆላመጣቸውም፣ አላለሳለሰም፤ ‹‹የምትሰሩት የማይገባ የማታለል ሥራ ነው፣ ድርጊታችሁ የሚያመለክተው ለመተጋገዝ አለመፈለጋችሁን ነው፣ ስግብግብነት ነው፣ በሕይወታችሁ የሚታየውን ይህንን መንፈሳዊ ስብራት መጠገን ያስፈልጋችኋል፡፡›› ብሎ በግልጽ አስረድቷቸዋል፡፡

- ከመጽሐፈ ነህምያ ምዕራፍ አምስት ቁጥር አንድ እስከ ቁጥር አሥራ ሦስት ድረስ የምንማረው እነዚህን ከላይ የተመለከትናቸውን የገንዘብ ቀውስን የምንፈታባቸውን መልካም የሕይወት ትምህርቶች ነው፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲

- ከቁጥር አሥራ አራት እስከፍጻሜው የምንማረው ነህምያ ስኬቱን እንዴት አድርጎ እንጠበቀው ወይም እንደ ተንከባከበው ነው፡፡
- በርካታ ሰዎች ስኬትን መጠበቅና መንከባከብ አይችሉበትም፡፡ ሳይመኩ፣ የተለየ ጥቅምን ሳይሹ፣ ብቃቴ ለዚህ አበቃኝ ሳይሉ ስኬትን መጠበቅ የሚሳናቸው ብዙዎች ናቸው፡፡
- እግዚአብሔር ከፍ ያደረጋቸው ሳይቀሩ በገንዘብ ሲበለጽጉ፣ ሥልጣን ሲያገኙ፣ ወዘተ ይበላሻሉ፡፡ ጌታችንም ‹‹ባለጠጋ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢሾልክ ይቀላል፡፡›› ያለው ለዚህ ነው፡፡
- ስኬትን መጠበቅ መንከባከብ የሚቻለው ማነው? ያለ እግዚአብሔር ወደ ከፍታው የሚወጣ ማንም የለም፡፡
- እግዚአብሔር ሳይመርጠው የሕዝብ መሪ የሚሆን የለም፡፡ የምንመረጠውም ጠንካራ ሠራተኞች፣ የንግግር ችሎታ ያለን በመሆናችን ወይም ባለን ችሎታ፣ በተማርነው ትምህርት፣ ወዘተ ሳይሆን ምርጫው ከላይ ስለሆነ ነው፡፡ ይህ ማለት ችሎታ ለማዳበር፣ ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን፣ … መማር የለብንም ማለት ሳይሆን እነዚህ ብቻቸውን ለከፍታችን ምክንያት አይሆኑም ለማለት ነው፤ ከፍታው የሚሆነው ከላይ ከእግዚአብሔር ነውና፡፡
- መጥምቁ ዮሐንስ ‹‹ከሰማይ ካልተሰጠው ሰው እንዳች ሊቀበል አይችልም።›› ***ዮሐ 3፡27 ::*** ያለን ስለዚህ ነው፡፡
- እግዚአብሔር ዮሴፍን ከወህኒ ቤት አውጥቶ በግብጽ ሁለተኛው ታላቅ ሰው ያደረገው በዚህ መንገድ ነው፡፡
- ዳንኤልንም ከአንበሶች ጉድጓድ አውጥቶ በባቢሎን ቤተ መንግሥት ሁለተኛው ታላቅ ሰው አድርጎታል፡፡
- በነህምያም የተደረገውም ይኸው ነው፤ ነህምያ ከፋርስ ወደ ኢየሩሳሌም የመጣው የኢየሩሳሌምን ቅጥር (ግንብ) በፕሮጀክት ለመሥራት ነበር፡፡ እግዚአብሔር ግን እንደነ ዳዊት፣ ሰሎሞን ንጉሥ አደረገው፡፡
- ‹‹ንጉሡም በይሁዳ ምድር ላይ አለቃ እሆን ዘንድ ካዘዘኝ ጊዜ ጀምሮ ከንጉሡ ከአርጤክስስ ከሀያኛው ዓመት እስከ ሠላሳ ሁለተኛው ዓመት ድረስ አሥራ ሁለት ዓመት ያህል እኔና ወንድሞቼ ለአለቃ የሚገባውን ስንቅ አልበላንም።›› ***ነህ 5፡14፡፡***

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲

- ትሑት - ራሱንም ዝቅ ያደረገ ሰው ከሆነ ስለምን አለቃ - እንደ ንጉሥ ሊሆን ቻለ? ለነህምያ የሚሻለውና የሚበልጥበትስ የትኛው ነው? የፋርስ ንጉሥ የጠጅ አሳላፊ መሆን ወይስ የይሁዳ ንጉሥ መሆን?
- ሙሴ እስራኤልን በበረሃ አርባ ዓመት ሲመራቸው ሞቱን እየተመኘ - እግዚአብሔርን እባክህን ግደለኝ እያለው እንደነበር ስለምናውቅ ለእኛ ቢሆን በፋርስ የንጉሡ ጩጅ አሳላፊነትን እንመርጥ ነበር፡፡
- ታዲያ ነህምያ ትሑት ሆኖ ሳለ ስለምን የአይሁድ አለቅነትን መረጠ? ‹‹ጻድቃን በበዙ ጊዜ ሕዝብ ደስ ይለዋል ኀጥኣን በሠለጠኑ ጊዜ ግን ሕዝብ ያለቅሳል።›› ***ምሳ 29:2*** እንዳለ ባለጠጎች ያልተመረጡት ኃላፊነት መቀበል ስላልወደዱነው፡፡
- ከባዱ ነገር የእስራኤል አለቃ (ንጉሥ) መሆን ሲሆን ቀላሉ ነገር በአንዱ ሐይቅ ዙሪያ ባዶ ቦታ ገዝተን፣ ቤት ሠርተን በዚያ የጡረታ ዘመናችንን ማሳለፍ ነው፡፡
- ከባዱ ነገር ነቢያቱን እነ ኢሳይያስን የገደሉትን አይሁድን መምራት ነው፡፡ ሙሴ እየመራቸው እንኳ የማይመቹ እርሱንም ብዙ ጊዜ የሚያስቆጡት ነበሩ፤ ታዲያ እነዚህን ማን ሊመራቸው ይፈልጋል?
- በርካታ ሰዎች ፖለቲካል ሳይንስ አጥንተው እንዲህ ዓይነት ኃላፊነትንም እንዲወጡ እናበረታታቸዋለን፡፡ ‹‹ፖለቲካ ቆሻሻ ነገር ነው፣ በደረሰበት አልደርስም…›› ማለት ለጊዜው - ለዘመኑ መፍትሔ አይሆንም፡፡
- ***ቁልፉ ችግር ባለ ሥልጣን ለመሆን አለመፈለጋችን ሳይሆን ኃላፊነት ለመቀበል አለመሻታችን ነው፡፡***
- ነህምያ እኔና ወንድሞቼ ለአለቃ የሚሆነውን አልበላንም አለ፡፡ አለቃ ስንሆን ወይም ወደ ከፍታው ስንወጣ አመጋገባችንም ሆነ የምግብ ፍላጎታችን ይጨምራል፤ መኪናዎቻችን፣ ቤታችን፣ ቁሳቁሶቻችን፣ … ይጨምራል፡፡ ነህምያ ግን አላደረግሁም አለን፡፡
- ነህምያ ባለሥልጣን ከመሆን ከሚገኘው ጥቅም ራሱን ለይቶ ኃላፊነትን ብቻ ተሸከመ፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፺

- ነህምያ ስኬታማ መሪ ለመሆን የበቃው በዚህ የተነሳ ነበር፤ ያለው የሚበቃው ቅምጥልነት የማያሸንፈው ነበርና፡፡
- ‹‹ከእኔ አስቀድመው የነበሩት አለቆች ግን በሕዝቡ ላይ አከብደው ነበር ስለ እንጀራውና ስለ ወይኑ አርባ ሰቅል ብር ይወስዱ ነበር ሎሌዎቻቸውም ደግሞ በሕዝቡ ላይ ይሠለጥኑ ነበር እኔ ግን እግዚአብሔርን ስለ ፈራሁ እንዲህ አላደረግሁም።›› ***ነህ 5፡15፡፡***
- በንጉሡ ዘንድ ያለው ገንዘብም በብላሽ የተገኘ ሳይሆን ከግብርና ከቀረጥ የተሰበሰበ ነው፡፡ በቅንጦች የምንኖር መሪዎች ከሆን ለቅንጦታቸን የሚከፍሉት ሕዝቦች እንደሆኑ ማወቅ ይኖርብናል፡፡
- ንጉሥ ሰሎሞን ውብ ቤተ መንግሥት ሠርቶ በዘመኑ ፍጻሜ በሺ ሴቶች ተከቦ ተገኝቷል፤ በመጨረሻ ዕዳውን የከፈሉት ግን ሕዝቦቹ ናቸው፡፡ ልጁ ሮብዓም ከነገሰ በኋላ ሕዝቡ አባትህ ሰሎሞን የጫነብንን ቀንበር አቅልልን ብለው ቢጠይቁት ‹‹አሁንም አባቴ ከባድ ቀንበር ጭኖባችኋል፥ እኔ ግን በቀንበራችሁ ላይ እጨምራለሁ አባቴ በአለንጋ ገርፎአችኋል፥ እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለሁ አላቸው፡፡›› ***ቀዳ ነገ 12፡14፡፡*** በማለት ለሕዝቡ ቀንበር ከማቅለል ይልቅ አከበደባቸው፡፡ ይህም የሚያመለክተን በመሪነትና በንጉሥነት መካከል ሰፊ ልዩነት እንዳለና ንጉሥ ሁሉ መሪ እንደሆነ አድርገን እንዳናስብ ነው፡፡
- ሰሎሞን አጉድሏል፤ ንጉሥነቱን ለምቾትና ድሎት ስላዋለው ነህምያ ከርሱ የተሻለ እንደነበር እናስተውል፡፡
- ስለ ሰሎሞን መልካም መሪ ነበር ብለን አልተማርንም፡፡ ምሳሌያዊ የጥበብ ንግግርን የሚወድ ንጉሥ እንጂ መሪ አልነበረምና፡፡ ስለዚህ ክርስቲያኖች ሆይ በተሰለፍንበት ነገር ሁሉ ለሌሎች መልካም ምሳሌ እንሁን፡፡
- ነህምያ ትሑት ወይም ለሕዝቡ የምጠነቀቅ ሆኜ ሳይሆን ግቤ እግዚአብሔርን ማክበር፣ ደስ ማሰኘት ስለሆነ እግዚአብሔርን እፈራዋለሁ አከብረዋለሁም አለ፡፡ ‹‹ከእኔ አስቀድመው የነበሩት አለቆች ግን በሕዝቡ ላይ አከብደው ነበር ስለ እንጀራውና ስለ ወይኑ አርባ ሰቅል ብር ይወስዱ ነበር ሎሌዎቻቸውም ደግሞ በሕዝቡ ላይ ይሠለጥኑ ነበር እኔ ግን እግዚአብሔርን ስለ ፈራሁ እንዲህ አላደረግሁም።›› ***ነህ 5፡15፡፡***

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲

- ‹‹ደግሞም አጥብቄ የቅጥሩን ሥራ ሠራሁ፥ እርሻም አልገዛንም ብላቴኖቼም ሁሉ ወደዚያው ወደ ሥራው ተሰበሰቡ።›› ***ነህ 5፡16፡፡*** ነህምያ ‹‹በሥልጣኑ ተጠቅመን መሬት ገዝተን ቢሆንስ? ያን ግዛ፣ ይሽኝ ጨምር፣ ያኛውን አስፋፋ ስንል እንገኝ ነበር፤ ይህም ግብ አይደለም፡፡›› አለ፡፡
- ‹‹ደግሞም በዙሪያችን ካሉት አሕዛብ ወደ እኛ ከመጡት ሌላ ከአይሁድና ከሹማምቱ መቶ አምሳ ሰዎች በገበታዬ ነበሩ።›› ***ነህ 5፡17፡፡*** በማለት ተራ መሪ አለመሆኑን እንድንረዳ ብሎም በዚህ ታላቅ ኃላፊነቱ በምቾት ቤተ መንግሥት ከመቀመጥ ይልቅ በዙሪያው መቶ አምሳ ሰዎችን በክብ ጠረጴዛ ሰበሰብሁ ብሎ ነገረን፡፡
- ምንም በርካታ ኃላፊነቶችና፣ ኀብኚዎች፣ ደጆ ጠኚዎች ቢኖሩብኝም ‹‹ከወፎችም በቀር ለአንድ ቀን አንድ በሬና ስድስት የሰቡ በጎች፥ በአሥር በአሥር ቀንም ብዙ ልዩ ልዩ ዓይነት ወይን ጠጅ ይዘጋጅልኝ ነበር ነገር ግን አገዛዝ በሕዝቡ ላይ ከብዶ ነበርና ለአለቃ የሚገባውን ስንቅ አልሻም ነበር።›› ***ነህ 5፡18 ፡፡*** አለ፡፡
- በመጨረሻም ‹‹አምላኬ ሆይ፥ ለዚህ ሕዝብ ያደረግሁትን ሁሉ ለበጎነት አስብልኝ።›› ***ነህ 5፡19፡፡*** በማለት የድካሙን ዋጋ ወደ ሚከፍለው እግዚአብሔር አመለከተ ልመናውንም አቀረበ፡፡
- ነህምያ ስለ አገልግሎት መርሑ ሲናገር ግቤ የእስራኤል ሕዝቦች፣ ቅጥሩን መሥራት ወይም አገልግሎት አይደለም ‹‹እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት፣ የእግዚአብሔርን ክብር መግለጥ ነው፡፡›› አለ፡፡
- ነህምያ ስኬታማ ብሎም በቀላሉ ልናገኘው የማንችለው በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኝ ፍሬያማ መሪ ሊሆን የቻለው በዚሁ ማንነቱ የተነሳ ነበርና በእውነትም ታላቅ አብነት የምናደርገው መሪ ነው፡፡
- ***ከነህምያ የመሪነትን ሕይወት ምንነት በጥልቅ ተረድተን የመሪዎችን በጎነት ገንዘብ ለማድረግ እንድንበቃ እግዚአብሔር በቸርነቱ ይርዳን እመቤታችንም በአማላጅነት አትለየን፡፡ አሜን!!!***

ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:

[kesisolomon4@gmail.com](mailto:kesisolomon4@gmail.com)

To get all the lessons, surf :

[www.zeorthodox.org](http://www.zeorthodox.org)